ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተግባር አሳይቶናል ምሳሌም ሆኖናል፡፡ ማቴ. 5፣43-48፤ 1ኛ ጴጥ፣ 2፣23፤ ሉቃ. 23፣24 ጠላትን ይቅር ብሏል በጠላትም እንዲሁ በነገ ነው እንጂ ምንም መነሻ አይኖረንም፡፡ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ከወደደን እኛ ደግሞ በአድን፣ ዘመድን፣ የቅርቡንም የሩቁንም ወዳጅንም ጠላትንም ቢሆን በአንድ ፍቅር መውደድ ይገባናል፡፡ ዮሐ. 3፣16፤ ሮሜ 5፣10 ለባልንጀራችን ያለን ፍቅር የልብ ስሜት ብቻ ሆኖ መቅረት የለበትም፡፡ በሥራ መገለጽ አለበት 1ኛ ዮሐ. 3፣8፤ ያዕ. 2፣15-16 ይኸውም ባልንጀራችንን በሥጋና በመንፈሳዊ ሕይወት በመርዳት ይገለጣል፡፡

## በሥጋዊ ሕይወት

- ለኑሮ የሚያስፈልገውን ነገር ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ማሟላት
- መብቱ እንዲጠበቅለት ማድረግ
- ጉዳት እንዳይደርስበት መጠንቀቅና መከላከል

## በመንፈሳዊ ሕይወት

- በጸሎት ማሰብ 2ኛ ጢሞ. 1፣3
- በጥሩ ተምሳሌትነት ወደ ቤተ እግዚአብሔር ማቅረብ ማቴ. 5፣16፤ 1ኛ ጴጥ. 5፣3
- በመንፈሳዊ ምክር ማነጽ ሮሜ. 12፣8

በዚህ ብቻ ሳይወሰን በፍቅር ለሌላው እራስን አሳልፎ እስከመስጠት ድረስ ሊቀጥል ይገባዋል፡፡ የፍቅር የመጨረሻው ደረጃ ይሄ ነው፡፡ ጌታችን ነፍሱን ስለወዳጆቹ አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ ሀግ ለማንም የለውም ብሏል፡፡ ዮሐ. 15፣13

## እንደራስህ ውደድ

ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚለው ትዕዛዝ ለባልንጀራችን የሚኖረን የፍቅር መጠን ምን ያህል መሆን እንደሚገባ ያስረዳል፡፡ ራሳችንን በምንወድበት መጠን መውደድ አለብን፡፡ የገዛ ሰውነቱን የሚጠላ የለም ኤፌ. 5፣30 በክርስትና ሃይማኖት የክርስቶስ አካል እንደሆነና እያንዳንዳችንም ብልቶች እንደሆንን ተገልጧል፡ 1ኛ ቆሮ. 12፣27

ስለዚህ አንዱ አንዱን አታስፈልገኝም ሊለው አይችልም፡፡ የራሱ ብልት ነውና፡፡ ሌላው ቢቸገር ቢታመም ቢደሰት የኛም ሊሆን ይገባል፡፡ ሌሎች ሊያደርጉልን የምንፈልገውን ነገር ሁሉ ለባልንጀራችን በማድረግ በተግባር እንግለጸው፡፡ ማቴ. 7፣12

## አንቀጸ ብፁዓን

አንቀጸ ብፁአን የተባለውን ትምህርት ያስተማረው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ትምህርቱም የሚገኘው በማቴዎስ ወንጌል ከምዕራፍ 5-7 ድረስ ነው፡፡ አንቀጸ ብፁአን የተባለውም ትምህርቱ በብፁአን አዋጆችን ስለሚጀምር ነው፡፡ አንቀጸ ብፁአን የተራራው ስብከትም ይባላል፡፡ ምክንያቱም ጌታ ትምህርቱን ሲያስተምር በእስራኤል ሰሜን በጥብርድያኖስ ባህር አጠገብ በገፍርናሆም አካባቢ በሚገኘው ሁለት ማይል ከፍታ ባለው ተራራ ኮረብታ ላይ ስለሆነ ነው፡፡ ማቴ. 4፣1-11

ይህ ትምህርት የሐዲስ ኪዳንን ሕግ የያዘ ነው፡፡ የብሉይ ኪዳን ሕግ በተራራ ላይ እንደተሰጠ ሁሉ የሐዲስ ኪዳንም ሕግ በተራራ ላይ ተሰጠ፡፡ የሐዲስ ኪዳን ሕግ በፊደል ሳይሆን በመንፈስ የሚመራ ነው፡፡ ስለዚህ የመንፈስ ሕግ ይባላል፡፡ ለክርስቲያን የሕግ ሁሉ ፍጻሜ ፍቅር ስለሆነ ሕጋጋቱን የሚፈጽመው በፍቅር ተገዶ ነው፡፡ እንዲያውም ከታዘዘው በላይ አትርፎ መልካምን ይሠራል፡፡ በዚህም ምክንያት የሐዲስ ኪዳን ሕግ ትሩፋት ይባላል፡፡ በብሉይ ኪዳን ሙሴና ነቢያት እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በማለት ሕግን ያስተምሩ ነበር ጻፎችና ፈሪሳውያንም

ከሙሴና ከነቢያት ሕግ ጠቅሰው ያለሥልጣን ያስተምሩ ነበር። ጌታችን ግን ሠራኢ ሕግ እንደመሆኑ መጠን እኔ ግን እላችኋለሁ እያለ እንደ ባለሥልጣን ያስተምራቸው ነበር። ማቴ. 7፤28-29 ስለዚህ ይህ የሐዲስ ኪዳን ሕግ በራሱ በባለቤቱ የተሰጠ የፍቅር ሕግ ስለሆነ ለብሉይ ኪዳን ሕግ መፈጸምያ ነውና የበለጠ ልንታዘዝለት ይገባል። ከማቴ. 5-7 ያለውን ክፍል ዋና ዋና ሕግጋትን አርእስት ሰጥተን ለይተን በማውጣት እንደሚከተሉት እንማራለን። እነርሱም፡ -

1. የብፁአን አዋጆች
2. ስድስቱ ቃላተ ወንጌል
3. ምፅዋት
4. ጸሎት
5. ጾም
6. ጠቃሚ ሕጎች ናቸው።

## 1ኛ የብፁአን አዋጆች ማቴ 5፤3-11

ይህ ክፍል የአንቀፀ ብፁአን የመጀመሪያው ክፍል ነው። አንድ ንጉሥ መንግሥቱ ከተደላደለ በኋላ ሕጉን በአዋጅ እንደሚገልጽ ሁሉ ጌታችንም ብፁአን የሚላቸውን ማን እንደሆኑ በአዋጅ መልክ ስለተናገራቸው የቤተክርስቲያን ሊቃውንትን የብፁአን አዋጆች ብለዋቸዋል።

ብፁአን ማለት ንዑዳን፣ ክቡራን፣ የተመሰገኑ፣ የታደሉ፣ የተባረኩ፣ ደስተኞች ማለት ነው። በዚህ ቃል እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተጠርታለች ሉቃ 1፤45-50 ቅዱስ ጴጥሮስም ተጠርቶበታል። ማቴ. 16፤17 ሌሎችም ቅዱሳንም በዚህ ሥም ተጠርተውበታል። ስለዚህ ቅዱሳን ለተጠሩበት ለዚህ ሥም መብቃት ታላቅ ክብር ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃሉን ሰምተው የሚያደርጉትን ማቴ. 13-23 ሳያዩ የሚያምኑ ዮሐ. 20፤29 ወደ ሠርጉ የተጠሩትን ራዕ. 19፤8 ብፁአን ናቸው በማለት አስተምሯል። ይህ አጠቃላይ አገላለጽ ያስተማረው ቢሆን አዋጆች ላይ ግን እነማን ብፁአን እንደሆኑ በዝርዝር ያስተምረናል። በማቴ. 5፤3-11 የተዘረዘሩት የብፁአን አዋጆች ሲቆጠሩ 9 /ዘጠኝ/ ናቸው። እነርሱም፡ -

1. በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁአን ናቸው መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና
2. የሚያዝኑ ብፁአን ናቸው መጽናናትን ያገኛሉና
3. የዋሆች ብፁአን ናቸው ምድርን ይወርሳሉና
4. ጽድቅን የሚራቡ የሚጠሙ ብፁአን ናቸው ይጠግባሉና
5. የሚምሩ ብፁአን ናቸው ይማራሉና
6. ልብ ንፁሐን ብፁአን ናቸው እግዚአብሔርን ያዩታልና
7. የሚያስታርቁ ብፁአን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና
8. ስለጽድቅ ብለው የሚሰደዱ ብፁአን ናቸው መንግስተ ሰማያት የእነርሱ ናትና
9. ሲነቅፏችሁና ሲያሳድዷችሁ በእኔ ምክንያት ክፉውን በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁአን ናችሁ ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ። ሐሴትም አድርጉ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያት እንዲሁ አሳደዋቸዋልና የሚሉት ዘጠኙ ናቸው።

### 1. በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁአን ናቸው መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና

... በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው ሲባል ድሆችና የመንፈስ ... ማስተዋል ይገባል:: የመንፈስ ድሆች ማለት ደግሞ መንፈሳዊው /የራሳቸው/ ከእውቀት ከግብዝነት ... የደኸዩ ምንም ያልተማሩ ማንነታቸውን የማያውቁ ማለት ሳይሆን ሁሉ እያላቸው ግን የራሳቸው ሳይሆን የእግዚአብሔር መሆኑን አውቀው እና አምነው ያላቸውን ሁሉ የእግዚአብሔር ነው ያሉ እኔ ደሀ ነኝ የሚሉ ማለት ነው:: ሰው ከእናቱ ሆድ ሲወጣ እራቁቱን ይወጣል ወደ መጣበትም እራቁቱን ይመለሳል:: እንዳች ነገር የራሱ የሆነ የለውም እዮብ 1፣21 እንኳን ያገኘነው ሀብት እውቀት፣ ደስታና ሰላም ቀርቶ እኛ ራሳችንም የእግዚአብሔር ነን ምድር መላዋን የእግዚአብሔር ናት መዝ 23፥1 እንዲሁም ከሆነ ፍፁም ድሆች መሆናችንን ልናምን ይገባል:: ሀብትና ባለጠግነት፣ ሥልጣንና ክብር ዕውቀት ደስታ፣ ሰላም ቢኖሩንም እንኳን የኛ ስላልሆነ እንደሰጠን ሁሉ እግዚአብሔር በተለያየ ምክንያት ሊወስደው ይችላል:: ታዲያ በዚህ ጊዜ በመንፈስ ድሆች የሆኑ እንደጻድቅ ኢዮብ "እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሳ የእግዚአብሔር ሥም የተባረከ ይሁን" ይላል ኢዮብ 1፣21 ከትንቱ ድኅነታቸውን አምነዋል:: ቅዱስ ዳዊት በጉባዔ ፊት እግዚአብሔርን ሲያመሰግን ክቡር ባለጠግነት ኃይልና ብርታት የእግዚአብሔር መሆኑን በመግለጽ ተናግሯል:: 1ኛ ዜና 29፥11-16 ስለዚህ በመንፈስ መሆን ከተሰበረ ልብ ይሄ ፍፁም ትህትና ነው:: የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ ደግሞ እግዚአብሔር አይንቅም:: ወደ ትህቃንና በቃሉም ወደሚኖሩት ሰዎች ይመለከታል:: መዝ. 50፣17፣ ኢሳ. 57፣15:: ሁሉንም ትተው ጌታችንን በመከተል እራሳቸውን ያደኸዩ የመንፈስ ድሆች ናቸው ጌታችን እራሱ ሁሉ የእርሱ ሲሆን እኛ ባለጠጎች እንድንሆን ስለ እኛ ደሃ ሆኗል:: 2ኛ ቆሮ. 8፣9

ከዚህ በመነሳት ሐዋርያትም ሁሉን ትተው ጌታን ተከተሉ:: ሁሉን ሲባል መጀመሪያ ራስን መካድ ከዚያም አባት፣ እናት፣ እህት፣ ወንድም ልጅንም ሐብትንም ንብረትንም መተው ነው:: ይህም ሊላውን ለማገልገል በወንጌል ምክንያት ነው እንጂ በሌላ ምክንያት አይደለም እንዲህም ሲባል እናጣዋለን ማለት ሳይሆን ሙሉ ሕይወታችን የሚያስፈልገን ከእግዚአብሔር ይገኛል ማለት ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ ድሆች ስንሆን ብዙዎችን ባለጠጎች እናደርጋለን:: አንዳች የሌለን ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው ብሏል:: 2ኛቆሮ. 6፣10:: እንግዲህ ያለን ነገር ሁሉ ለእኛ አለመሆኑን ካወቅን የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ልንሰጥ ይገባልና:: እግዚአብሔርንም በድሆች ብድራት በማይመልሱ ይገለጣል:: እንዲህ ካደረግን መንግሥት ሰማያት የእኛ ትሆናለች:: ማቴ. 25፣35-46 ተመልከት::

2. የሚያዝኑ ብጹአን ናቸው መጽናናትን ያገኛሉና

እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚያዝኑ እንጂ የዓለምን ሐዘን እያሰቡ የሚያዝኑትን አይደለም ስለ ኃጢአት ተጸጽቶ ለንስሐ ማዘን ተገቢ ነው:: የእዚህ ዓይነቱ ጸጸት የሊለበተን ወደ መዳን የሚያደርሰው ንስሐ ያደርጋል፣ የዓለም ሐዘን ግን ሞትን ያመጣል 2ኛቆሮ. 7፣9-10:: ከዚህም ሌላ ለጠፉት ሰዎችም ልናዝን ይገባናል:: ጌታችን ብዙ ሕዝብ ባየ ጊዜ እረኛ እንደሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው:: በተለይም ደግሞ ከሕገ እግዚአብሔር ርቀው በኃጢአት ለጠፉ ሰዎች ልናዝንና ልናለቅስ ይገባል::

ሐዘን በሦስት ዓይነት ይከፈላል::

1. ስለራስ ኃጢአት እያሰቡ ማዘን ማልቀስ መሳሌ፡ – አዳም፣ ቅ. ጴጥሮስ
2. ስለባልንጀራ ኃጢአት እያሰቡ ማዘን ማልቀስ ምሳሌ፡– ሳሙኤል ለሳኦል 1ኛሳሙ. 16፣ 1 - 3
3. ስለሞተ ወልደ እግዚአብሔር እያሰቡ ማልቀስ

ጌታችን ስለ ኢየሩሳሌም ከተማ አልቅሷልና። ሉቃ 19፥41 ይህ ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሐዘን ነው በዚህ ዓይነት የሚያዝን ሰው በክርስቶስ ይጽናናል። ትሑስ ጴጥሮም በለቅሶ የሚዘሩ በደስታ ይለቅማሉ በማለት ገልጿል። ይኸውም በዚህ ዓለም በክርስትና ምክንያት በልዩ ልዩ ፈተና ሳዘኑ ሰዎች ነው። ቅዱስ ጴጥሮስም ለምስጋና፣ ለክብር ለውዳሴ የሚያበቃ መሆኑን ገልጿል። 1ኛጴጥ. 1፥ 6 - 7

በማናቸውም ዓይነት ይሁን ሰዎች እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ካዘኑ፣ ካለቀሱና ካነቡ የሚያጽናና አምላክ፣ የፍቅር አባት ጌታ እግዚአብሔር እንባቸውን ያብሳል። ራዕ. 7፥17 ያጽናናቸውማል።

3. <u>የዋሆች ብፁዓን ናቸው ምድርን ይወርሳሉና</u>

ይህ ቃል "ገሮች ምድርን ይወርሳሉ" ተብሎ በመዝሙረ ዳዊት ተገልጿል። መዝ፡ 36፥11 የዋህነት ገርነት ነው። ቂምን አለመያዝ የበቀልን ብድራት አለመመለስ የዋሕነት ነው። ያለውን ሁሉ በነፃ የሚሰጥ ቢወስድበትም ጨምሮ የሚሰጥ የዋሕ ሰው ይባላል። የጌታችንንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእኔ ተማሩ እኔ የዋሕ፣ በልቤም ትሁት ነኝና ለነፍሳችሁም እረፍት ታገኛላችሁ ብሎናል። ስለዚህ የዋህነትን ከአባታችን መማር አለብን። እርሱ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም ሲይዙትም እራሱን አሳልፎ ሰጣቸው መከራ ሲቀበል አልዛተም 1ኛጴጥ. 2፥23 ራሱን ባዶ አድርጎ ይኸውም ለመስቀል ሞት እንኳን የታዘዘ ሆነ። ፊልጵ. 2፥8 በነገር ሁሉ እንዳደረጉት ሆነላቸው። ይኸውም በየዋሕነት ያደረገው ነው። የዋሕነት እንደሕፃን መሆን ነው። መንግሥተ ሰማያትም እንደነርሱ ላሉት ናትና። ማቴ 18፡3 ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስ እንዳደረገው ለክፋት ነገር ነው እንጂ በአእምሮ ሕፃናት መሆን አይገባም። 1ኛ ቆሮ 14፥30። በአእምሮ የበሰላችሁ ሁኑ ተብሏልና። የዋሕነት ቂልነት ማለት ሳይሆን ለእግዚአብሔር እራስን ማዋረድ፣ ማስገዛት ማለት ነው በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኗል። 1ኛቆሮ. 1፥21። የቀህነት ከመንፈስ ፍሬዎች አንዱ ነው በተለያየ ቦታ ትህትና፣ ትዕግሥት፣ ፍቅር፣ በጎነት፣ ቸርነት፣ ከተባሉ ከመንፈስ ፍሬዎች ጋር አብሮ ተዘርዝሯል። ኤፌ.4፥2፤ ገላ.5፥22፤ ቆላ. 3፥12፤ ቲቶ 3፥12 ተመልከት። የዋህነትን ከክርስቶስ ተምረን የዋሆች ከሆንን ብፁዓን የሚለውም ቃል ከጌታ ተሰጥቶናል። እንደተከፉ ቃሉ የምንጠብቃት አዲስ ሰማይና ምድርን ያወርሰናል። 1ኛጴጥ.3፥13፤ ራዕ. 21፥1

4. <u>ጽድቅን የሚራቡ፣ የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው ይጠግባሉና</u>

ጽድቅ ማለት ሕግን መፈጸም፣ እንደ ሕግ መኖርና መመራት ትክክለኛነት እውነተኛነት ማለት ነው። ሮሜ 3፥11 ጻድቅ የለም አንድስ እንኳ ይላል። ለምሳሌ ኖኅ፣ ሎጥ፣ ዘካርያስ ሌሎችም ጻዲቃን ተብለዋል ዘፍ 6፥9፤ ሉቃ. 1፥6፤ 2ኛጴጥ 2፥8 ነገር ግን ሁሉም ጉድለት ተገኝቶባቸዋል። ስለዚህም እኛ ምንም የጽድቅ ሥራ ብንሠራ ጉድለት አያጣንም። ኢሳይያስ እንደተናገረው የምንሠራው ጽድቅ የመርገም ጨርቅ ነው። ኢሳ. 4፥6 እግዚአብሔር በባሕርይው ጻድቅ ነው። ዕዝ. 9፥9፤ 1ኛጢሞ. 4፥8 ፍጹም ጽድቅ የሚገኘው ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ ነው። ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ሲል ከእግዚአብሔር የሚገኘው ጽድቅ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ስለጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲነገር የሚጠራበት ስሙን "እግዚአብሔር ጽድቃችን" ተብሎ እንደሆነ ተገልጧል። ኢሳ. 23፥ 5-6፤ ፡ ዮሐ. 8፥31፤ ጌታችን በዚህ ዓለም ሳለሁ እኔ እውነት/ጻድቅ/ ነኝ ብሏል። ዮሐ. 14፥6 ስለዚህ ጽድቅን መራብና መጠማት ማለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መናፈቅ እንደ እንጀራና እንደ ውኃ መፈለግ ማለት ነው። እርሱም እራሱ ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ በማለት ተናግሯል። ዮሐ.

6፤32-51 የተራቡና የተጠሙ ሁሉ ወደእርሱ መጥተው እንዲጠግቡና እንዲረኩ በተለያየ ጊዜ ጥሪውን አስተላልፏል፡፡ ኢሳ.55፤1፤ ዮሐ.6፤35-37፤ ራዕ. 22፤14 ስለዚህ የሥጋ ፍላጎታችን የሚራበውንና የሚጠማውን ኃጢአት ትተን ጽድቅን የምንራብና የምንጠማ ከሆነ እንጠግባለን እንረካለን፡፡ ቅዱስ ዳዊት ዋልያ ወደ ውኃ ምንጮች እንደሚናፍቅ አቤቱ ነፍሴ አንተን ትናፍቃለች ነፍሴ ወደ ሕያው አምላክ ተጠማች መቼ እደርሳለሁ የአምላክን ፊት መቼ አየዋለሁ.. መዝ. 41፤1-2 ቅዱስ ጳውሎስም ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፡፡ ከሁሉም ይልቅ የሚሻል ነውና ብሏል፡፡ ፊል. 1፤23 ጽድቅን መራብና መጠማት ማለት እንዲህ ዓይነት ናፍቆት ነው፡፡ ስለ እንደዚህ ዓይነት ጽድቅ መከራን ስትቀበሉ ብፁአን ናችሁ በማለት ተገልጧል፡፡ 1ኛጴጥ. 3፤14 ይህንንም ይዘን ወደ ጌታ ብንቀርብ እንጠግባለን እንረካለን ማለት፣ የጽድቅ አክሊል እንቀዳጃለን 2ኛጢሞ. 4፤8 ጻድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንወርሳለን፡፡ 1ኛ ጴጥ. 3፤13፡፡

## 5. የሚምሩ ብፁአን ናቸው ይማራሉና

የሚምሩ ሲል የሚራሩ፣ ቸር የሆኑ ይቅርታ የሚያደርጉ ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር በምህረቱ ባለጠጋ ነው፡፡ ኤፌ. 2፤4 ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን ይወዳል፤፤ ሆሴ. 6፤6፤ ማቴ. 12፤7 ስለዚህም እግዚአብሔር ከእኛ የሚሻው ምሕረት እንድናደርግ ነው፡፡ ሚክ፡ 6፤8 ለምሳሌ፡- ዳዊት ለሳኦል፤ ዮሴፍ ለወንድሞቹ ምሕረት እንዳደረጉ እኛም ለበደሉን ምሕረት ይቅርታ ማድረግ አለብን፡፡ ዘፍ. 50፤15-24፤ 1ኛሳሙ. 24፤17-21፤ 1ኛሳሙ. 26፤21-25፡፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃጢአተኞች ከቀራጮች ጋር በልቷል፡፡ ይህም ምሕረትን አድርጎላቸው ነው፡፡ "እንዲያውም ለጠያቂት ሂዱና ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕት አይደለም" ያለውን ተማሩ ብሏቸዋል፡፡ ማቴ. 9፤13 ጌታችን ብዙ ኃጢአተኞችን ምሕረት አድርጎላቸዋል፡፡ ማርያም መግደላዊት፣ ዘኪዎስ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ በመስቀል ለሰቀሉትም ይቅርታን ምሕረትን ለምኖላቸዋል፡፡ ሉቃ. 23፤34፡፡ እኛም ምሕረትን የምናደርግ ከሆነ ምሕረትን እናገኛለን፡፡ እግዚአብሔር ይቅር የሚለን እኛም ይቅር ስንል ነው፡፡ ማቴ. 6፤15፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ምሕረት ለድሆች ማድረግና መራራት እንዲሁም መስጠት ነው፡፡ ይኸውም ምጽዋት ነው፡፡ ምሳ. 11፤21-31፤ ሆሴ. 14፤3፤ ሮሜ 5፤6፤ ማር. 10፤46-52፤ ማቴ. 18፤21-35 ተመልከቱ፡፡

ስለዚህ ጠላት እንኳን ቢበድለን ይቅር ልንለው ቢራብ ልናበላው ቢጠማ ልናጠጣው ቢቸገር ልንረዳው በአጠቃላይ ምሕረት ልናደርግ ያስፈልጋል፡፡

## 6. ልበ ንፁሖን ብፁአን ናቸው እግዚአብሔርን ያዩታልና

ልብ ማለት የሰው አእምሮ ፈቃድ ሃሳብና ስሜት ነው የሰው ልብ የሚቆሸሸው በክፉት ነው፡፡ መልካም ሰው ከልቡ መዝገብ መልካም ነገርን ያወጣል፡፡ ክፉ ሰው ከልቡ መዝገብ ክፉ ነገርን ያወጣል፡፡ በልቡ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና፡፡ ማቴ. 12፤34-35፡፡ ሰውን የሚያረክሱ በሰው ልብ ውስጥ ያሉ ክፉቶች ማር. 7፤21-23፤ ማቴ. 15፤16-20 ላይ ተዘርዝሯል፡፡ እነርሱም ክፉ ሃሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምዥት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸው ልባችንን ከነዚህ ነገሮች ብናነጻ ብፁአን እንሆናለን፡፡

እግዚአብሔር በሥጋዊ ዓይን እንደማይታይ የታወቀ ነው፡፡ በልባችን ግን እግዚአብሔርን ማየት እንችላለን፡፡ ይሁንና እግዚአብሔርን ለማየት እንድንችል ልባችን ንፁህና ቅዱስ መሆን አለበት ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ ትቀደሱ ዘንድ ፈልጉ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ

ይሚችል የለምና ተብሎ ተጽፏል፡፡ ዕብ. 12፤14 የቀደሙ ነቢያት በተለየ መልክ እግዚአብሔርን ሊያዩ ችለዋል ልቦናቸውና መንፈሳቸውን ንጽህ በየገድራግ ነው፡፡ ዘኍ.12፤6-8፤ ኢሳ. 6፤1 የእግዚአብሔር ቃል የእኛም ልብ ከኃጢአት ንጹህ የጠራ መሆን እንደሚገባው ሲያስረዳ "እናንተ ኃጢአተኞች እጃችሁን አንጹ ሁለት ሃሳብም ያላችሁ እናንተ ልባችሁን አጥሩ ይላል" ያዕ. 4፤8 ብዙዎች ግን በአፍ ከምንናገረውና በሥራ ከምንገልጸው ይልቅ በልባችን ያለው ክፋት እጅግ ብዙ ነው፡፡ ስንናዘዝም የልባችንን ኃጢአት እንሰውራለን፡፡ እግዚአብሔር ግን ልብን ይመረምራል ኩላሊትንም ይፈትናልና የተሰወረውን ሁሉ ያውቃል፡፡ ኤር. 17፤9-10 ስለዚህ እግዚአብሔር በኃጢአት የቆሸሸውን ልብ እንዳያገኝብን በንስሐና በመናዘዝ እራሳችንን እናንጻ፡፡ 1ኛዮሐ. 1፤7 እግዚአብሔር ለዚህ እንዲያበቃን እንደ ቅዱስ ዳዊት "አቤቱ ንጹህ ልቦናን ፍጠርልኝ የቀናውን መንፈስ በውስጤ አድስ" ብለን ልንጸልይ ይገባናል፡፡ መዝ. 50፤10

## 7. የሚያስታርቁ ብፁአን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና

ማስታረቅ በተጣሉ ሰዎች መካከል ጥልን አጥፍቶ ሰላምን መፍጠር ማለት ነው፡፡ የጥልን ግድግዳ አፍርሶ ሰውንና ሰውና ቦታን፣ ሰውና መላእክትን፣ ሰውንና ሰውን፣ ሕዝብንና አሕዛብን፣ ሰውንና እግዚአብሔርን ያስታረቀው የእግዚአብሔር ልጅ እየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ኤፌ. 2፤14-17 ዛሬም መካከለኛ ሆኖ የተጣሉትን የሚያስታርቁ ብፁአን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና፡፡

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጣሉትን ሁለታቸውንም ሆኖ አስታርቋል፡፡ መካከለኛ የተባለውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ 1ኛጢሞ. 2፤5-7፤ ገላ. ፤19-20 እኛም የተጣሉትን ስናስታርቅ ፍርድ አጉድለን አንዱን አሳዝነን አንዱን አስደስተን ሳይሆን በመካከለኝነት ሊሆን ይገባል፡፡ የሁለቱም ምሥጢር የምናውቀውና ለሁለቱም እኩል የምንፈርድ መሆን አለበት፡ እርቅ እንዲፈጠር ሊከፈል የሚገባ ምንም ዓይነት ካሳ ቢኖር ልንከፍል ይገባል፡፡ ጌታችን ጠላቶቹ ሳለን ያስታረቀንም የታረቀንም እራሱን ለሞት አሳልፎ በመስጠት የደሙን ካሣ በመክፈል ነው፡፡ ሮሜ. 5፤10፤ ቆላ. 1፤10-22 የተጣሉት ሁለቱም ሥጋና ነፍስ ሊሆኑ ይችላሉ አንድ ሰውና አንድ ሰው ለሆኑ ይችላሉ፣ ማኅበርና ማኅበር፣ ሀገርና ሀገር ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እርስ በርሳቸው ከተጣሉ ከእግዚአብሔር ጋር ይለያያሉና፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ሰዎችን የምናስታርቀው በቅዱስ ቃሉ አማካኝነት መክረን አስተምረን በመመለስ ነው፡፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ካስታረቀ በኋላ የማስታረቅን ቃል በሐዋርያትና ተከታዮቻቸው አኑሯል፡፡ 2ኛቆሮ. 5፤19፡፡ ያ ቃል ዛሬም ስላለ በተለይም ወንጌል የሚሰብኩ ሰዎች ይህን የማስታረቅ አገልግሎት ተግተው ሊፈጽሙ ይገባቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋርም አስታርቀዋል፡፡ ዘኁ. 14፤13-20፤ 1ኛጢሞ. 2፤1 ተመልከቱ፡፡ በዚህ ዓይነት እርቅን የሚመሠርቱ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ፡፡

## 8. ስለጽድቅ ብለው የሚሰደዱ ብፁአን ናቸው መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና

ስደት በተለያዩ ምክንያት ከሚያውቁት ከተወለዱበት ሀገር፣ ከሚያውቋቸው ሰዎች ተለይቶ በመሸሽ መሄድ ነው፡፡ ከዚህ በላይ ስደት ሲባል በየምክንያቱ የሚደርሰውን መከራና ስቃይ ያሳያል፡፡ ክርስቲያን መሰደድ የሚገባው በጽድቅ ምክንያት ሊሆን ይገባል እንጂ

በኃጢአት፣ በውሸት፣ በፖለቲካ መሆን የለበትም። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም መድኃኒት ለመሆን በተወለደ ጊዜ በሄሮድስ ተንኮል ምክንያት ከእናቱ ጋር ሆኖ ወደ ግብፅ ተሰዶ ነበር ማቴ. 2፣13-18 በማስተማር ዘመኑም ችግር ሲገጥመው ከአንዱ ሀገር ወደ አንዱ ሀገር ይሄድ ነበር። ዮሐ. 4፣1-2 ለደቀመዛሙርቱ ሲያስተምር ባንዲቱ ከተማ መከራ ቢበዛባችሁ፣ ወደ ሌላይቱ ሽሹ ብሏል። ማቴ. 10፣23 በዚህም መሠረት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማስመሰል እንድንኖር ሳይሆን ስለ ጽድቅና ስለ እውነት ብለን መሰደድ እንደሚገባን በተግባርም በቃልም አስተምሮናል ማለት ነው። ቅዱስ ጳውሎስም በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ ብሏል። 2ኛጢሞ. 3፣12 ሐዋርያት ወንጌልን የሰበኩት እውነትነትን የተናገሩት በብዙ ስደት ነው። የመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን እስጢፋኖስ በተገደለ ጊዜ ታላቅ ስደት ገጥሟት ነበር። ሐዋ. 8፣10 ከዚህ በኋላ በዘመነ በማዕታት ሁሉ ቤተክርስቲያን በስደት ነበረች። ስለዚህ ዛሬም ቢሆን በጽድቅ ምክንያት ስደት ቢገጥመን ብፁአን እንባላለን። ሀገርና ቦታ፣ ቤትና ንብረት ቢቀርብንም እግዚአብሔር ግን የማታልፈውን ሀገርና ቦታ ርስትና ቤት የሆነችውን መንግሥት ሰማያትን ያወርሰናል። ጌታችን ስለዚህ ሲያስተምር ስለ ስሜ ቤቶችን ወይም ወንዶችን ወይም ሚስትን ወይንም ልጆችን ወይንም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል። የዘለዓለምን ሕይወት ይወርሳል ብሏል። ማቴ. 19፣29

ይህ አንቀጽ ስለ ጽድቅ መሰደድ መነቀፍንም በውሸት መታማትንና መጠላትንም ያጠቃልላል። ከዚህ ሌላ በስደታችሁ ሁሉ ደስታ እንዲኖረን ሐሴትን እንድናደርግ ያስተምራል። ሐሴት ማለት እጥፍ ድርብ ደስታ ማለት ነው። ደስ ሲለን የሚገባው ዋጋችን በሰማያት ታላቅ ስለሆነ ነው። የቀደሙ ነቢያትም እውነትን በመናገራቸው ምክንያት ተነቅፈዋል፣ ተጠልተዋል፣ ተሰደውማል። ዕብ. 11፣32-38 መድኃኒታችን በአሕዛብ ሁሉ ስለስሜ ስላስታማራችሁ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ ብሏል። ማቴ. 10፣22 ጌታና ሐዋርያትም በኋላ ሰማዕታትም እስከ ሞት የደረሱት በመነቀፍ፣ በመጠላትና በመሰደድ አስቀድመው ብዙ መከራ ካዩ በኋላ ነው። ዛሬ ግን ብዙዎች ደስ የሚላቸው ሲወደሱና ሲወደዱ ብቻ ነው። ነገር ግን በክርስቶስ ምክንያት ሲነቀፉ መከራ ሲደርስባቸው ደስ ሊላቸው ይገባል። በመከራችሁ ሁሉ ደስታዬ ከመጠን ይልቅ ይበዛል በማለት ቅዱስ ጳውሎስ ተናግሯል። ስደት የሚሰጠውን ክብር ከዋጋ በላይ ስለሆነ ታላቅ ክብር ነው።

ሰድስቱ ቃላተ ወንጌል

እንደ እግዚአበሔር ቅዱስ ፈቃድ ለመኖር የሚያስችሉ የሰው ልጅ ወደ ሕይወት ጎዳና ለመራመድ መዘጋጀት ምክንያት የመሆኑ ሰድስቱ ቃላት የተባሉ ሕግጋት ይገኛሉ። እነኝህም የሥነ ምግባር መሠረታዊ ሐሳች ናቸው። ክርስቶስም አጽንቶ ተናገራቸው። እነኝህን ሕግጋት በግልጽ ማወቅና መጠበቅ አለብን። ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማግኘት ከፈለግህ ሕግጋትን መጠበቅ አሰቡ ብሎናል ማቴ. 19፣16 የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ለሐዲስ ኪዳን ሕግጋት መሸጋገሪያ ሆነው አጥረው ተጠቃለው ከበድም ብለው ሐዲስ ኪዳን መታወቂያ መለያ ሕግ ናቸው።

እነዚህም፡ -

1. በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል።